# **የአቶ በረከት በክሱ ጥፋተኛ መባልና የዶክተር ዐብይ ተቃዋሚ አልባ መሆን ያሳስበኛል** ክፍል ሁለት

በአዲስ ተስፋ

ባለፈው በክፍል አንድ ምልከታየ ሁለት ስጋቶች አሉኝ በማለት የአቶ በረከት ጥፋተኛ መባል ማለትም በተጠረጠረበት አዳጋች እንደሚሆን የራሴን ምሳሌ በማቅረብ አንባቢዎቼን ለመሞገት ሞክሬያለሁ። ሁለተኛው ደግሞ ዶክተር አብይ ተቃውሞ አልባ እየሆኑ መምጣታቸው አሳስቦኛል ብያለሁ። በዚህ ረገድ ለማለት የፈለግሁት ቀደሞ የገባቸው ወገኖች እንዳሉ አውቃለሁ ። በዚህም ረገድ ማጠቃለያ አልሰጠሁም። ነገር ግን የዶክተር አብይ ፓርቲ ማለትም ኢህአዴግ የዘራውን ክፉ ዘርና የቀበረውን የጊዜ ቦምብ ነካ ለማድረግ ሞክሬያለሁ። ይህ የአስተዳደር ፍልስፍና ማለትም በዘርና በቋንቋ የተመሰረተው አከላለልም ሆነ የነገዶች ከአገር አንድነት ይልቅ መንደራዊ ማንነታቸውን ማጉላት አባዜ ከስሩ ተመንግሎ አልተጣለም። ህጋዊ እውቅናውም እንዳለ ነው። ዶክተር አብይ በግል ማንነታቸው የፈለጉትን ያህል ኢትዮጵያን የሚዎዱ ቢሆኑ፣ የቱንም ያህል አንድነትን የሚፈልጉ ቢሆኑ የቆሙበትና የሚመሩት ድርጅት ግን አገራችንን የከፋፈለ ሌቦች ሌብነታቸውን በጎሳቸው ማንነት የሚደብቁበት ያንኑ አስተሳሰብ ነው። ህገመንግስቱ ይከበር እየተባለ የሚጮህለትም የዚህ ፓርቲ ህገመንግስት ነው። ሌላው ቀርቶ እውነትን ለማፈላለግ ይቋቋም የተባለውን የክልሎች የወሰን ኮሚሽን እንኳ አንቀበልም በማለት በአደባባይ እነ ደብረጽዮን እያወጁ ነው።የህወሃት ገመና አደባባይ መውጣት የጀመረው ዛሬ ባይሆንም የህገመንግስቱ ይከበር ጩኸት ግን የውሸት መሆኑን ራሳቸው በአደባባይ በሚዲያ ሸረው አሳይተውናል። **ደብረጽዮን ሌቦችን እታደጋለሁ ብሎ አለም እንዲነቀው የሚያደርግ ሁለት ታላላቅ የህግ ጥሰቶች በአንድ ሳምንት ብቻ አሳይቶናል።** እነሱ ያወጡትን ህግ ማለቴ ነው። **አንደኛው ህግ ይከበር እያለ ራሱ ህግን የጣሰበት መንገድ የትግራይ ክልል ያሳለፈው ለክልሎች የወሰን ኮሚሽኑ አልገዛም የሚል መግለጫ ነው።** በአፓርላማ በአብላጫ ህግ የጸደቀን ህግ አባል የክልል መንግስታት መቃወምና በክልሎች እንዳይፈጸም ይከለክላሉ የሚል ስልጣን አልተሰጣቸውም። የትግራይ ክልል በክልላችን ይህ ህግ ተግባር ላይ አይውልም ብቻ ሳይሆን በሌሎች ክልሎችም እንዳይተገበር ያሳስባል ይላል። መሉ በሙሉ የፌደራል መንግስቱን ስልጣንና ሃላፊነት በራሱ ፈቃድ የትግራይ ክልል መንግስት እንደወሰደ ከዚህ መግለጫ መገንዘ ይቻላል። **ሁለተኛውና አሁንም እነ ደብረጽዮን የተላለፉት ህግ በህገ መንግስቱ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች የራሳቸውን መብት በራስ የመዎሰን እስከመገንጠል ይችላሉ የሚለውን ሃሳብ በመጠቀም መግንጠላችንን ከማንም አንጠይቅም መብታችን ነው በማለት ዶክተር ደብረጽዮን መናገራቸው ነው።**ማን አልብኝነት ፤ ህጉን የሰራሁት እኔ ስለሆንኩ የመሻር መብቴ የተጠበቀ ነው እንደማለት ማለት ነው። ነገር ግን ራሳቸው ደብረጽዮን ያወጡትን ህገ መንግስት አላነበቡትም ወይም አያዉቁትም። አንድ ክልል ለመገንጠል እጅግ በርካታ ሂደቶችን ማለፍ ይኖርበታል። እንግዲህ ደብረጽዮን እንደ ጠጅቤት ወሬ መገንጠሌን ማንንም ማስፈቀድ አይጠበቅብኝም ብለው የተናገሩበት ስለመገንጠል የሚያወራው የህገመንግስት ክፍል አንቀጽ 39 ላይ ይገኛል። አንቀጽ 39 ቁጥር 4 እንዲህ ይነበባል። የብሔር ብሔረሰቦች ሕዝቦች የራስን እድል በራስ የመወሰን እስከ መገንጠል መብት ከስራ ላይ የሚውለው

ሀ) የመገንጠል ጥያቄ በብሔር ብሔረሰቡ ወይም በሕዝቡ የሕግ አውጪ ምክር ቤት በሁለት ሶስተኛ የድምጽ ድጋፍ ተቀባይነት ማግኘቱ ሲረጋገጥ

ለ) የፌደራሉ መንግስት የብሔር የብሔረሰቡ ወይም የሕዝቡ ምክር ቤት ውሳኔ በደረሰው በሶስት አመት ጊዜ ውስጥ ለጠያቂው ብሔር ብሔረሰብ ወይም ሕዝብ ህዝበ ውሳኔ ሲያደራጅ

ሐ) የመገንጠሉ ጥያቄ በሕዝበ ውሳኔው በአብላጫ ድምጽ ሲደገፍ

መ) የፌደራሉ መንግስት መገንጠሉን ለመረጠው ብሔር ብሔረሰብ ወይም ሕዝብ ምክርቤት ስልጣኑን ሲያስረክብ

ሠ) በሕግ በሚወሰነው መሰረት የንብረት ክፍፍል ሲደረግ ነው።

እንግዲህ ሁሉ ነገር አልቆ የፌደራል መንግስቱ መገንጠሉን ለመረጠው ብሔር ብሔረሰብ ወይም ህዝብ ምክርቤት ስልጣኑን አላስረክብም ቢል መገንጠሉ ተፈጻሚነት እንደማይኖረው ቁጥር 4 በተራ ቁጥር መ) ማንበብ እንችላለን።

ይህ ሁሉ እያለ ነው እንግዲህ የደብረጽዮን መንግስት መገንጠሌን ማንንም አላስፈቅድም በማለት በአደባባይ የደነፋው። **ዶክተር አብይ ይህንን የደብረጺዮን ድርጊት አመጸኞች በማለት መወንጀል ብቻ ሳይሆን በሀገር ክህደት ወንጀል የመክሰስ ህጋዊ መሰረት እንዳለው ይታወቃል።** ነገር ግን ዶክተር አብይ በይፋ የክልሎችን አወቃቀርም ሆነ ርዕዮተ አለማቸውን ለመቀየር ምንም አይነት ምልክት አላሳዩም። ነገር ግን በሚዎስዱት እርምጃ ሁሉ ድሮ ተቃዋሚ ናቸው የምንላቸው ሙሉ በሙሉ በሚመስል መልኩ ሲደግፏቸው እንጂ በምክንያት ሲቃወሟቸው አናይም። ሁሉም አጨብጫቢ ሁሉም ደጋፊ ብቻ ሆኗል። **ብዙዎቻችን እንደምንለው የተረቀቀው ህገመንግስት ህዝብ ያልተስማማበት ፣ ህዝብን ያላሳተፈ ስለሆነ በተልይም አንድን ማህበረሰብ ነጥሎ ያገለለ ስለነበር ለውጥ አለ ከተባለ ይህ ኢህጋዊ ህግ መታገድ ነበረበት።** ይህ ባልሆነ ሁኔታ ሁሉም ደጋፊ መሆኑ በእርግጥም ያሳስበኛል።የርዮተ ዓለም ተቃዋሚ አለመኖሩ ደግሞ አሳሳቢ ብቻ ሳይሆን የዘር አከላለሉን እንቃወማለን በማለት መናገሩ ብቻ ዋጋ የለውም። በአንድነት ስም የተደራጁም ሆነ ኢትዮጵያን የሚዎዱ ሁሉ የኢህአዴግ ተቃዋሚ መሆን ነበረባቸው። አሳዛኙ ነገር ግን ለአመታት ወያኔን እቃወማለሁ የሚለው ኢሳት ራሱ ዶክተር አብይ የሚዎስዷትን እያንዳንዷን እርምጃ እንደ ገደል ማሚቶ እየተከታተለ መልካም እርምጃ ነው ሲል መስማት አስቂኝ ብቻ ሳይሆን የህወሃት የውጪ ክንፍ አስመስሎታል። አቶ በረከት በስልጣን ላይ በነበረበት ጊዜ የገዥውን ፕሮፓጋንዳ ማሽን በሶስት ይከፈው ነበር። በራሱ በገዥው ፓርቲ ውስጥ ፓርላማው መቶ በመቶ ደጋፊ ቢሆንም በውጪ ባሉ የህዝብ ግንኙነትና በአመለካከት ደረጃ ካድሬዎች በሶስት የተከፈሉ ነበሩ። **አንደኛው ገዥው ፓርቲ የሚያውጣቸውን ህጎች ፣ ፖሊሲዎችና መመሪያዎች ያለምንም ተቃውሞ የሚደግፍና** ስለተፈጻሚነታቸው በርትቶ የሚሰራ ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ስለ ወጣው ህግ መልካምነት የሚያዎራ የሚደግፍና የሚጽፍ ነው። **ሁለተኛው ደግሞ በሁሉም አቅጣጫ ተቃዋሚ ሆኖ የሚቀርብ የሚተችና ይህንንም ሃሳቡን የሚጽፍ የሚያስተጋባና በሃገሪቱ የሃሳብ ነጻነት እንዳለ የሚያስመስል ነገር ግን ደግሞ በመጀመሪያ ቡድን ሁሌም የሚነቀፍ የተለያየ ታርጋ የሚለጠፍበት ነበር።** ይህ ቡድን እጅግ ጽንፈኛ የሆኑ ጋዜጦችና የሚዲያ አውታሮች ሳይቀሩ አሉት። በሚዲያ ህጉ የተከለከሉ ሃሳቦችን ሳይቀር ያነሳሉ። ግን አይከሰሱም፣ ቢከሰሱም ለይስሙላ ነበር። ለምሳሌ በ2002 መጀመሪያ አካባቢ ፍትህ ሚኒስተር የጋዜጦችን ባለቤቶችና ዋና አዘጋጆች ሰብስቦ አንድም በአሸባሪነት የተፈረጀን የፖለቲካ ፓርቲም ሆነ ድርጅት መልእክት ማስተላለፍ፣ የፓርቲ መሪዎችን ወይም ደጋፊዎችን ቃለመጠይቅ ማድረግ በህግ የተከለከለ መሆኑን ይህንን አድሮጎ የሚገኝ ሁሉ እንደሚከሰስና እንደሚቀጣ የህትመት ወይም የብሮድካስት ድርጅቱም እንደሚዘጋ ከባድ ማስጠንቀቂያ አስተላለፈ። ይህ በሆነ በማግስቱ አውራ አምባ ታይምስ የተባለው ጋዜጣ የዶክተር ብርሃኑ ኢንተርቪው ብሎ በሙሉ ገጽ ሽፋን ይዞ ወጣ። በወቅቱ ዶክተር ብርሃኑ አሸባሪ ተብሎ በፓርላማ የተፈረጀን ድርጅት እንደሚመሩ ይታዎቃል። አውራምባ ታይምስም ጀግና በመባልም ይወደስ ነበር። በነገራችን ላይ በወቅቱ ዋና አዘጋጁ ከፍ ት ህ ሚኒስተር በተሰጠው ማሳሰቢያ መሰረት ይህ በህግ ያስቀጣናል እኔንም ያሳስረኛል ብሎ ሲከራከር የወቅቱ ስራ አስኪያጅ ዳዊት ከበደ ለዋና አዘጋጁ የ ፳ ሺህ ብር ስጦታ እንዲሰጠው እንደሚደረግ እንደነገረውና ዋና አዘጋጁም ባለመስማማቱ በእለቱ እንደተቀየረ መረጃው አለኝ። የዋና አዘጋጁን ስም መጥቀስ አስፈላጊ ስላልሆነ አልጠቀስኩም። ሌላም ሌላም በህግ የተከለከሉ ነገሮችን የሚያወጡ ነብሩ። ይህ እንግዲህ የራሱ የኢህአዴግ ክንፍ ነው። በዚህ ቡድን ያሉ ታቃዋሚ የሚል ታርጋ የተለጠፈባቸው ነገር ግን የአገዛዙ ጋሻጃግሪዎች በጋዜጦች ላይ የግለሰቦችን ስም ያጠፋሉ ፣ የፈለጉትን ባለስልጣን ይሰድባሉ፣ የግለሰቦችን የስልክ ውይይት ሳይቀር የተጠለፈ መልእክት በጋዜጣ ያሳትማሉ። ሌሎች ህግ አክብረው የሚሰሩ ከመንግስት ጋር መሞዳሞድ የሌላቸው ግን በዜናዎቻቸው ርእስ ሳይቀር ይከሰሳሉ። **ሶስተኞቹ ደግሞ መንግስት ያለውን የማይደግፋም የማይቃዎሙም ናቸው።** እነዚህኞቹ ምንም አይነት አመለካከት ብታንጸባርቁ አይቃወሟችሁም አይደግፏችምም ። ስለዚህም የአቶ

በረከት ስትራቴጂ በራሳቸው ውስጥ አንዱን በአንዱ እያሰለሉ መኖር ነበር። በርካታ ምሳሌዎችን ማቅረብ ቢቻልም አንድ እና ሁሉም የተሸዎደበት ታሪክ ላንሳና ይህንን ሃሳብ ልቋጨው ለቋጨው። አሁንም የብዙ መረጃዎች ምንጭ ሆኖ እያገለገለ ያለው የአቶ አማራ አረጋዊ ሪፖርተር ግን ወደር የሌለው ድራማ የተሰራበት ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ህዝብ ምንም የማያውቅ መሆኑን ለማሳየት የሚሞክሩበት የፕሮፓጋንዳ ማሽናቸው ነበር። ሪፖርተር አቶ በረከትን በሃይለኛው የሚተች ጽሁፎችን ያዎጣል። የሳምሶን ማሞ ኢትዮ ቻናል የተባለ ጋዜጣ ደግሞ የአቶ አማረን ጉድ በየሳምንቱ ይዘረዝራል።ስለዚህም ለኢትዮጵያ ህዝብ አቶ በረከትና አቶ ስብሃት (በሪፖርተር በጣም ከፍ ከፍ የሚደረጉ) የማይታረቁ ጠላቶች እንደሆኑ እንዲነገር የደረጋል። አቶ በረከትና አቶ አማረ የማይታረቁ ጠላቶች ናቸው እየተባለ ይወራል። አቶ አማረና አቶ ሳምሰን ቢገናኙ ይገዳደላሉ እየተባለ የነገራል። እውነታው ግን ይህ ሁሉ ስራ የአቶ በረከት መሆኑና ሁሉም ሰዎች የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች መሆናቸው ነው። ኢህአዴግ ማለት ይህ ነው ፣ ይህንን ድርጅት ደግሞ አሁን እየመሩት ያሉት ዶክተር አብይ ናቸው። ታዲያ ሁሉም ሲደግፋቸው ስርዓቱን ከስር ገንድሰው እንዲጥሉ የሚያስገድ ዳቸው ተቃዋሚ መጥፋቱ እንዴት አያሳስበኝ?ወድ አምባቢዎቼ ከላይ የአንዳንድ ሰዎችን ስም ያነሳሁት በብዙ የሚታዎቁ ስለሆኑና ለኢህ አዴግ የፕሮፓጋንዳ ማሽን ሆነው ማገልገላቸው የአደባባይ ምስጢር ስለሆነ እንጅ መረጃዎችን ብንመዝዛቸው ዛሬ አቶ በረከትን የሚረግሙ ጀግና ያምንላቸው የሚድያ ሰዎች በሙሉ በሚባል ደረጃ በሰንሰለቱ ውስጥ የነበሩ ናቸው። አንዱን መጥቀስ ከፈለግን እየተያያዘ እየተያያዘ የምንወዳቸው ሰዎችን ማጥለቅለቁ አይቀርም። በግልጽ በሌብነትና በሰብአዊ መብት ጥሰት የተረጋገጠባቸውን ለፍትህ ከማቅረብ ውጪ ግለሰቦችን ነጥለን ለመለየት የምናደርገው ውጊያ የትም አያደርሰንም። ይልቁንም የዶክተር አብይን መንግስት በተጨባጭ የሚቃዎም አማራጭ ፓርቲ ያስፈልገናል። የዶክተር አብይ ተቃዋሚ አልባ መሆን ግን ለአገራችን ጥሩ ዜና ሳይሆን የምንጠላቸውን ግለሰቦች ከእከሌ ጋር አይናቸው በሚል የግለሰቦች ማጥቂያ ሜዳ ብቻ ነው የምናገኘው። ለምሳሌ አትሌቶቻችንን ፣ አርቲስቶቻችንን፣ ምሁሮቻችንን በተናጠል የምናደርገው ማግለል ርእዮተ አለማዊ ተቃውሞ አይደለም። ባለፉት ሃያ ሰባት አመታት አውቆም ይሁን ሳያውቅ በእነ አቶ በረከት የጥልልፎሽ ተንኮል ያልተነካ ዜጋ አናገኝም። ይህ ተንኮል ግን መቀጠል የለበትም። የተወሰኑትን ለማግዘፍ ሌሎችን ደግሞ ለማኮሰስ በተቀነባበረ መንገድ የሚሰራውን ኢህአዴግን ከስሩ የሚቃዎም ህገ መንግስቱን እስከ ማሻር ድረስ የሚያስገድድ የዘር ፖለቲካውን ማስቀረት ብቻ ስይሆን በህግ የሚያግድ ብርቱ ተቃውሞ ያስፈልገናል። በአቶ በረከት ዙሪያ ያለኝም ስጋት ሆን ተብሎ ትቃዉሞን ለማብረድ የተውጠነጠነ ፖለቲካዊ ጨዋታ እንዳይሆን እጠራጠራለሁ።ሌላው የአቶ በረከት አንድ ባህርይ ለመነጋገሪያ የሚሆን ርእስ በየጊዜው የማምረት ችሎታው ነው።

በተለይ ይህንን ጨዋታ ውጪ ያለውን ዲያስፖራ ትኩረቱን ለመውሰድ በደንብ ይጠቀምበት ነበር። ከመንግስት ሾልኮ የወጣ ምስጢር በማለት የራሱ የስልክ ንግ ግር ሳይቀር ሪከርድ እያደረገ ዜና ተቃዋሚ በሚባሉ ሚዲያዎች እንዲሰራ ያደርግ ነበር። ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያክል ከአዲሱ ለገሰ ጋር ያደረገውን የስልክ ውይይት ለኢሳት እንዲደርስ ያደረገበት መንገድ ፣ የመለስ ዜናዊ ሞት ሁለት ወር ወደ ሚጠጋ ጊዜ ዜና እንዲሆን ያደረገበት መንገድ፣ የሃይለማርያም ደሳለኝን ሹመት ህውሃቶችና የተወሰኑ ቡድኖች እንደተቃወሙ በማድረግ ከወር ያላነሰ ጊዜ ዜና ሆኑ እንዲቆይ ያደረገበት መንገድ፣ በተጨማሪም አንድ የመንግስት ባለስልጣን የሆነ ጥፋት እንዳጠፋ በማስመሰል በ ሪፖርተር ወይ በሌላ ጋዜጣ ረዥም ጊዜ ርእስ እንዲሆን በማድረግ የብዙሃኑን ትኩረት ለማሳብ አጀንዳ በመስጠት ጠበብቱ አቶ በረከት በሙስና ክሱ መርጃ ይገኝበታል ብየ ለማሰብ ተቸግሬያለሁ። ብዙዎቻችን ያልገመትነው ራሱ ይሰራው እንደነበረው ያለ ፖለቲካዊ ፊልም እንዳናይ በእርግጥም እሰጋለሁ። ጨረስኩ።

አገራችንን ኢትዮጵያን እግዚአብሔር ይባርክ!

አዲስ ተስፋ

ፌብሩዋሪ 2019 ዓም